# ያልቅስ ተጎልቶ

ስም እያበላሹ ፣ ጭቃ እየተቀባ
ብሶትና እሮሮ ፣ በረባ ባልረባ
እንደ ሞኝ ዘፈን ፣ ሁሌ ያይኔ አበባ
አሀያው እያለ ፣ ዳውላው ሰለባ ።

አቶ አይጥ በበላ ፣ ዳዋ እየተመታ
በወሬ ቱማታ ፣ ጽኑ ላይረታ
ሀሰት ፣ እውነት ላይሆን ፣ ቢዳከር ጧት ማታ
ችግሩ አይከላ ፣ አንድ ውል አይፈታ ።

ያፍ አርበኛ በዝቶ ፣ የሚያውደለድሉ
መቋጠሪያ የሌለው ፣ ያልታወቀ ውሉ
እብጠት ሲሰማቸው ፣ ሞቷል እንዳላሉ
አልሆንም ሲላቸው ፣ ጣት ይቀስራሉ ።

ያራዳ ጨዋታ ፣ ሁለት ባላ መትከል
አንደኛው ሲሰበር ፣ አንዱ ላይ መንጠልጠል
እንዳገኙ መዝገን ፣ እንደ ጅብ ፣ መዘንጠል
ሰውን ያለስራው ፣ እንዳሻ ማብጠልጠል ።

ለራሱ እየዋሸ ፣ ውስጡን አደንቁሮ
ያላዋቂ ፣ አዋቂ ፣ ገብቶ ተደንቅሮ
መሳሳትን ማመን ፣ ወንጀል መስሎት አፍሮ
እንደ አሮጌ ሸክላ ፣ ሁሌም ዞሮ ዞሮ
ድማሙ ፣ ድማሙ ፣ ሰለቸን ዘንድሮ ።

ሞቷል ፣ ባለበት አፍ ፣ አለ ፣ ብሎ ሰግቶ
ከጠላቱ በላይ ፣ ሞተ ያለውን ፣ ፈርቶ
መለየት አቅቶት ፣ ጠላቱን ለይቶ
መደንገጥ ዘወትር ፣ ሁሌ እንቅልፉን አጥቶ
ወዳጁን ያጠቃል ፣ አንደበቱን ከፍቶ
ትግል ከመሰለው ፣ ያልቅስ ተጎልቶ ።

ታዛቢው ... July 6, 2010